ለቀስተ ደመና ሬድዮ ከመላ ኢትዮጵያ ሶሻሊስት ንቅናቄ ሥነ ጽሁፍና ዝግጅት ክፍል
የቀረበ ትችት

# ተወራርደናል

ነጻ ምርጫን አስመልክቶ ዛሬ በሃገራችን ያለው ሁኔታ ሁለት ገጽታዎች አሉት። አንዱ ግልጽ የሆነ ገጽታ ዛሬ በኢትዮጵያ ነጻ ምርጫ ለማካሄድ ከዛሬ አምስት ዓመት ይበልጥ የተመቻቸ ሁኔታ አለመኖሩ ነው። ሁለተኛው ግልጽ ሁኔታ ደግሞ የኢትዮጵያ ዲሞክራቶች በዚህ በነጻ ምርጫ ጉዳይ የዛሬ አምስት ዓመት ያልነበራቸውንና በታሪካችንም ለመጀመሪያ ጊዜ ዝርዝር የሆነ አቋም ይዘው በኢተፖድህ አማካኝነት በመንቀሳቀስ ላይ መሆናቸው ነው።

መላ ኢትዮጵያ ሶሻሊስት ንቅናቄ ከሌሎች የኢትዮጵያ ዲሞክራቶች ተባብሮ ኢተፖድህን ሲመሰርቱ ህብረታችን ለኢትዮጵያ ህዝብ የገባው ቃል ኪዳን ደግሞ የዚያኑ ያህል ግልጽ ነው። በዚህ የጋራ ሰነድ ዙሪያ የህብረታችን አባል ድርጅቶች ተጋግዘውና የሃገሪቱንም ዲሞክራቶችና አገር ወዳዶች፣ በነሱም አማካኝነት መላውን የኢትዮጵያን ህዝብ ለትግል አንቀሳቅሰው፣ ዛሬ የሰፈነውን የነጻ ምርጫ እድል ደብዛው የጠፋበትን ሁኔታ ለመቀየርና በህብረተሰባችን ለዲሞክራሲ የሚያደላ የኃይል ሚዛን ለመፍጠር የተደረገ ቃል ኪዳን ነው።

ይህ ለዲሞክራሲ የሚያደላ የኃይል ሚዛን በረዥም ጊዜ ጥራትና ቆራጥነት በማይለየው ተጋድሎ የሚገኝ ህዝባዊ ድል እንጂ ከህዝብ ተነጥለው ውር ውር በሚሉ ኃይሎች የአንድ ሰሞን ግርግር የሚከሰት ጉዳይ አይደለም። የኢተፖድህ መሥራች ድርጅቶች አምና በፓሪስ ከተማ ባጸደቁት "የዲሞክራሲ ሂደትና የነጻ ምርጫ ትልም" በተሰኘው ሰነዳቸው ከዚህ የድል ምእራፍ ለመድረስ አስፈላጊውን የመጀመሪያ እርምጃ ወስደዋል። ከእንግዲህ የሚቀረው፣ ያለ እንዳች ወለም ዘለም፣ በዚህ ሁሉን አቀፍ በሆነ ሰነድ ተመርኩዞ ወቅቱንና በሃገራችን ያለውን የኃይል ሚዛን ከቁጥር የሚያስገባና ከሁሉም በላይ ደግሞ፣ ለዚህ ድል አስፈላጊ የሚሆነውን የህዝብ ተሳትፎ ከእለት እለት እየጨመረ የሚሄድ የትግል ታክቲክ እየቀየሱ፣ ውስብስቡን የትግል ምእራፍ መያያዝ ነው።

ከዚህ አንጻር ሲታይ፣ ባለፈው መስከረም በፍራንክፈርት ከተማ የተካሄደው የኢተፖድህ ሁለተኛ ጠቅላላ ጉባኤ፣ ላለንበት የትግል ምእራፍ የሚመጣጠንና ከሁሉም በላይ ደግሞ፣ የኢትዮጵያን ህዝብ ከዳር እስከዳር ለትግሉ እንዲነሳሳ ሁኔታዎችን የሚያመቻች፣ ውሳኔ አሳልፎ መጠናቀቁ የሃገራችን ዲሞክራቶች በህብረት ትግል ስልት ብስለት እያገኙ መሄዳቸውን፣ ህዝባችንን አንቀሳቅሰው እስካልተንቀሳቀሱ ድረስ ትግሉ ሁሉ በአየር ላይ ተንሳፎ የሚዋልል፣ ትርፉ ድካም እንደሆነ መረዳታቸውን የሚመሰክር መልካም ክስተት ነው።

የኢተፖድህ ጉባኤ፣ ምንም እንኳን በሃገራችን ለነጻ ምርጫ የተመቻቸ ሁኔታ እንደሌለ ጠንቅቆ እንደተረዳ ቢያስታውቅም፣ ምንም እንኳን የምርጫ ህጉ፣ የምርጫ ቦርዱና አጠቃላዩ የምርጫ ሂደት በአንድ አምባገነናዊ ፀረ-ዲሞክራቲክ ኃይል ሙሉ ቁጥጥር ስር እንደሆነ ባይስተውም፣ ምንም እንኳን ማንም ይሳተፍ ማንም የዚህ ምርጫ ተብየ ግርግር ውጤቱ ምን እንደሆነ በግልጽ የታወቀ ቢሆንም፣ ከወዲሁ "አንሳተፍም" የሚለውን ቀላልና በትግል ያኮረፉ የሚመስለውን አቋም አላንጸባረቀም። በግንቦቱ የወያኔ ምርጫ አንጻር የተወሰደው እጅግ የጠራና ታግሎ ማታገል በሚል ስትራቴጂ ላይ የተገነባው የኢተፖድህ አቋም፤

1ኛ/ በኢትፖድህ ሰነድ የተዘረዘሩት መስፈርቶች በተግባር ሊተረጎሙ የሚችሉት፣ ባለጉዳዩ የሆነው የኢትዮጵያ ህዝብ፣ ከዳር እስከዳር ተንቀሳቅሶ፣ ፀረ ዲሞክራሲያዊውን አገዛዝ በማንኛውም መስክ የሚሞክራቸውን የሸፍጥ ሂደቶች እየታገለ ሲያከሽፋቸው ብቻ እንደሆነ ይገነዘባል።

2ኛ/ ከዚህ በመነሳት በግንቦት ወር የኢህአዴግ መሪዎች የሚሞክሩት የተጭበረበረ የምርጫ ሂደት፣ በኢትዮጵያ ህዝብም ፊት ሆነ በዓለም አቀፉ ኮሙኒቲ ደረጃ ምንም ዓይነት ተቀባይነት እንዳያገኝ ማድረግ ለቀጣዩ ትግል ወሳኝነት እንደሚኖረው ጠንቅቆ ይገነዘባል።

3ኛ/ ከነዚህ መሠረታዊ ግንዛቤዎች በመነሳት ይህንን የሸፍጥ ሂደት ሙሉ በሙሉ ለማጋለጥና የኢትዮጵያ ህዝብም በኢትፖድህ አማራጭ ዙሪያ በመሰባሰብ እንዲታገለው ለመቀስቀስ፣ በህጋዊነት በሃገር ውስጥ የሚንቀሳቀሱ የኢትፖድህ አባል ድርጅቶች የወያኔ/ኢህአዴግ ምርጫዎች በሚካሄዱባቸው የምርጫ ቀበሌዎች በሙሉ እየተገኙ፣ ህዝቡም ይህንን ሂደት ነቅቶ እንዲታገለው ለማነሳሳት የሚያስችላቸውን ምዝገባ እንዲያካሂዱ ወስኗል።

የኢትፖድህ ጠቅላላ ጉባኤ፣ ከዚህ በማያያዝ አቅም ከሌለ አቋም ብቻውን የትም እንደማያደርስ በመገንዘብ፣ ለዚህ ዘመቻ በውጭም፣ በውስጥም ያሉ የሃገራችን ዲሞክራቶች ባላቸው አቅም ሁሉ፣ በገንዘብም ሆነ በቁሳቁስ፣ በፖለቲካም ሆነ በዲፕሎማሲ መስክ እንዲድግፉት ጠይቋል።

ይህ ውሳኔ የኢትፖድህ አባል ድርጅቶች የወያኔን የምርጫ ሂደት በየምርጫው ቀበሌዎች እየተገኙ እንዲያጋልጡ የሚያስችላቸውን ምዝገባ ያካሂዱ ይላል እንጂ ተመዝግበው ምርጫ ውስጥ ይሳተፉ የሚል እንዳይደለ ግልጽ ነው። በዚሁ የፍራንክፈርቱ ሰነድ ላይ በትክክል እንደተቀመጠው ግንቦት ላይ የወያኔ አመራር ይህንን የህዝብ ትግል ከመጤፍ አልቆጥር ብሎ የለመደውን የሸፍጥ ሂደት ከገፋበት የተመዘገቡት የኢትፖድህ አባል ድርጅቶች ለወያኔ ግርግር በሻማ ያዥነት እንዳይሰለፉ ብቻ ሳይሆን የኢትዮጵያ ህዝብም በዚሁ ተጋልጦ እርቃኑን በቀረው ፊዝ ከመሳተፍ እንዲቆጠብና ዓለም አቀፉም ኮሙኒቲ እንዲያወግዘው ጥሪ እንደሚያደርግ በግልጽ አስጠንቅቋል።

ይህ ሁሉ ትክክለኛ አቋም በእርግጥ ትክክለኛ የሚሆነው የህዝብ ወገን ነን የሚሉ ኢትዮጵያውያን በሙሉ በነቃና ጥራት ባለው ሁኔታ በሚንቀሳቀስ ህዝብ ኃያልነትና አይበገሬነት እንደተደረገ የፖለቲካ ውርርድ አድርገው እስከቆጠሩት ድረስ ብቻ ነው። በህዝብ ኃያልነት ተወራርደናል ብለን ከዚህ እስከ ግንቦት ድረስ ህዝባችንን በያለበት ለመድረስና ለማንቀሳቀስ የሚያስችለን ስትራቴጂ ከቀየስን ይህንን ውርርድ እናሸንፋለን። ይህንን ካላደረግን ተመዝግበን አልተመዘገብንም፣ ምርጫ ተሳተፍን አልተሳተፍን/ቦይኮት አደረግን/ ዞሮ ዞሮ ትግሉ በወያኔ ዙሪያ በተኮለኮሉ፣ ባላቸው ገንዘብ፣ ማቴሪያል፣ ሠራዊት፣ ፖሊስና ቢሮክራሲ በሚተማመኑ ጥቂት ጸረ ህዝቦችና ለሃገርና ለህዝብ ካላቸው በጐ ምኞት ሌላ ምንም መሞርኮዣ በሌላቸው ጥቂት ዲሞክራቶች መሃል የሚካሄድ ትግል ይሆናል። ከዚህ ውርርዳችን ያለጥርጣሬ ተሸንፈን እንወጣለን።

ይህ እንዳይሆን የኢትፖድህ አባል ድርጅቶች ብቻ ሳይሆኑ በጠቅላላው የኢትዮጵያ ዲሞክራቶችና አገር ወዳጆች ህዝባዊ አማራጫችንን ይዘው ወደ ህዝቡ እንዲገቡ አስፈላጊ የሚሆነውን የፖለቲካ፣ የዲፕሎማሲ፣ የፋይናንስና የቁሳቁስ አቅም ለማጐልበት ሳይውሉ ሳያድሩ መንቀሳቀስ ይኖርባቸዋል። ይህንን ካደረግንና በሚቀጥሉት ወራት ለዚህ የታገሉ ማታገል ራእዩ ኢትፖድህ የሚቀይሳቸውን ታክቲኮችና ስልቶች ደግፈን

ከተንቀሳቀሰን ፊቱንም ቢሆን ኢተፖድህ በኢትዮጵያውያን ተማምኖ ባደረገው የፖለቲካ ውርርድ በአሸናፊነት ይወጣል። ይህንን አንገብጋቢ ተግባርና ይህንን ትክክለኛ ህዝባዊ ሂደት፣ በተለያዩ ድብቅ አጀንዳዎች ምክንያት ለማዝረክረክ የሚሹ አዝማሚያዎች ከተከሰቱና የሃገራችን ዲሞክራቶች ውኸንብር ውስጥ ወድቀው፣ ጥሪያችንን ማዳመጥ ካቃታቸው፣ ይህ የኢተፖድህ አቋም ለኢትዮጵያችን ያለንን በጎ ራእይ ከማንጸባረቅ አልፎ የሚያመጣው ምንም ፋይዳ አይኖረውም።

መላ ኢትዮጵያ ሶሻሊስት ንቅናቄ ይህ ወደ ህዝብ የመግባት ዘመቻ የሱም የቆየ ራእይ በመሆኑ በዚህ ሂደት ውስጥ በሃገርም፣ በውጭም በሚገኙ አባላትና ደጋፊዎቹ አማካኝነት ከተቀሩት የኢተፖድህ አባል ድርጅቶች ጐን ያለ እንዳች ማወላወል በግንባር ቀደምነት ለመታገል፣ ከመቸውም ይበልጥ ዝግጅት ያደረገና በማድረግ ላይ መሆኑን በዚህ አጋጣሚ ለማረጋገጥ እንወዳለን።

የመላ ኢትዮጵያ ሶሻሊስት ንቅናቄ
ሥነ ጽሁፍ ዝግጅት ክፍል።

ጥቅምት ፬ ቀን ፲፱፻፺፪ ዓ.ም.

DISTRIBUTED BY
THE N. AMERICAN
OFFICE BRANCH
c/o P. O. BOX 21644
WASHINGTON, DC 20009-1644

ቀስተ ዳመና ሬዲዮ
Radio Rainbow Radio Arc-En-Ciel

C/o P.O.BOX 140. 140. 53056 BONN GERMANY-FAX (49) 228/61-23-81

ቀስተ ዳመና ሬድዮ በዓለም አቀፍ ደረጃ፣ ማለትም በየሣምንቱ አንድ ጊዜ ወደ ኢትዮጵያ፣ ምሥራቅ አሜሪካ ጠረፍና አውሮፓ የሚተላለፍ የአማርኛ ፕሮግራም ነው።